## ኢትዮሚዲያ
## ርእሰ አንቀጽ
# እንካ -ይህንን ያዝ
ትርጉም ኦላና ኦብሴ


አምባሳደር
ሳሙኤል አሰፋ

“ማታለልን እንዲህ እንደዛሬ ሳንካነው ፤ድሮ በመጀመሪያ ስንለማመደው፤ አቤት እንዴት ድርና ማጉን አወሳሰብነው’’ ይህ አባባል በአሜሪካ የመለስ ዜናዊ አምባሳደር ሳሙኤል አሰፋ በቅርቡ ለWAMU ሬዲዮ አስተናጋጅ ለኮጆ ናምዲ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ ያንፀባርቃል። ኢትዮጵያ ለቡና ጥራት ያደረጋችውን አስተዋፅኦ በማስመልከት ከአስተናጋጁ ጋር መጠነኛ ጭውውት ካደረጉ በኋላ ቀጣዩ የኣምባሳደሩ ስራ ከተለያዩ ጠያቂዎች የሚቀርቡትን የእንጉርጉሮ ዜማዎች ማዳመጥ ነበር።

ስልክ ደዋይ ጥያቄ አቀረበ።
‘’በኦሮሞ ብሔረሰብ ላይ ለምን ይህን ያህል ጭቆና ይደረጋል? የፓለቲካ ነፃነት ለምን የለም? በኦሮሞዎች አካባቢ በተለየ ሁኔታ የመብት ረገጣው ለምን ከፋ? ይህን ቢመልሱልኝ፤ በነዚህ አካባቢ ነፃ ምርጫ ይደረጋል ወይስ በዋና ከተማው ላይ ያለው የአናሳው መንግስት ወኪል ነው የሚሾመው?’’

አምባሳደሩ ጥያቄውን በቅጽበት በምሁራዊ ስልት አጣጥመው እንደ አሲድ የሚቆጠቁጠውን እውነት ለማለዘብ ትርጉም በማይሰጥ የዲፕሎማቲክ ፍሬ ፈርሰኪ ሽፋፍነው ለማለፍ ሞክረዋል።

‘’ለነዚህ መጠነ ሰፊ ለሆኑ ክሶች መልስ መስጠት ያስቸግራል ። ማለቴ - እም - ጥያቄው በማንኛውም የሃገሪቱ ክፍል ህግ ተጥሷል ወይ ከሆነ፤ የህግ መጣስ የለም ቢባል ሊገርመኝ ይችላል። በእኛ ሃገር ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላም ሀገር ውስጥ የመብት ረገጣ (የህግ መጣሰ) የለም ቢባል ይገርመኛል። ዝርዝር መረጃዎቹ ቢቀርቡ ኖሮ በዝርዝሩ ላይ መወያየት ይቻል ነበር። እም-እዚህ ላይ ለዚህ እንደምሳሌ የሚያገለግሉ ባሕርያት አልቀረቡም። ምክንያቱም ባሕርያት ንድፍን ያመለክታሉ ንድፍ ደግሞ የዚህ ዓይነት ስልት ሆን ተብሎ መያዙን አመልካች ነው። ሆኖም ግን

አልቀረቡም። አንድ ሰው ለምን የሰው ልጅ መብት የለም የሚል ድፍን ያለ ጥያቄ ቢጠይቅ ጥያቄውን መመለስ ይከብዳል። <u>ምንም የሚያዝ የሚጨበጥ መረጃ ከጠያቂው አላገኘሁም"</u>

አምባሳደሩ እነዚህ በእስቴት ዲፓርትሜንት የተዘጋጁትን የመጋቢት 2000 የሰዉ ልጅ መብት ዘገባ ውስጥ የተካተቱን እውነታዎች እንደ ዋቢ መያዝ ይችሉ ነበር። "በታህሳስ 24 2000 በኦሮሚያ ክልል በጉዌ ከተማ በጉዌ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፓሊስ ባደረገው ድንገተኛ ወረራ ሁለት ተማሪዎችን ገድሏል፤ ብዙ ተማሪዎችንም ደብድቧል፤ አስሯል። አንዳንዶቹ ተለቀዋል ሌሎች ከአመት በኋላም እስር ቤት ናቸዉ። ገዳዮቹ ለምንድን ነዉ ለፍርድ ያልቀረቡት?"

"በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪ የነበረዉ በላቸዉ እንዳለው ቢተዉ በታህሳስ 26 ቀን 2000 ዓ ም  በፓሊስ ተገድሏል። "የበላቸዉ ገዳይ ተይዞ ለምን ለፍርድ አልቀረበም?

" በሚያዚያ 1998 በኦሮሚያ ክልል በናዝሬት ከተማ በፓሊስ የተገደሉትን የእነ አለሙ ተስፋ፤ ታሪኩ ያኪሶ እና መንሱር ሙሰማ ጉዳይ ለምን ተደዳፍኖ ቀረ?" ታሪኩን፤ መንሱርንና ሙሰማን የገደሉት ፓሊሶች ለምን ታስረዉ ለፍርድ አልቀረቡም?"

በሚያዚያ 1998 በጌዶ ከተማ ገበያ ላይ 15 ሰዎችን ገድሎ 37 ሰዎችን ካቆሰለዉ ፍንዳታ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አራት የኦሮሞ ብሄራዊ ንቅናቄ (ONC)አባላት ታስረዋል"እነዚህ የኦሮሞ ብሔራዊ ንቅናቄ አባለት ፍርድ ቤት የመቅረብ መብታቸው ተጥሶ ለምን እስከአሁን በወህኒ ቤት እንዲቆዩ ተደረገ?

የአነስተኛ ንግድ ባለቤት የነበረው ግርማ ተስፋዬ አያና ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ አለህ በሚል ክስ ከሀምሌ 4 ቀን  ከተያዘ ጅምሮ የደረሰበት አልታወቀም። እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የጅማ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበረው በፈቃዱ ቡልቲ ሜራ በተመሳሳይ ክስ ከሀምሌ አንድ ከታሰረበት ቀን ጀምሮ የደረሰበት አይታወቅም። ግርማና በፍቃዱ የት ናቸው?

"ፓሊስ በመስከረም ሶስት በኦሮሚያ ክልል የሚአ አውራጃ የሕዝብ ተወካይን አቶ ወጋየሁ ደጀኔንና ቤተሰቦቻቸውን ደበደበ። ፓሊስ ግለሰቡን ማዋከብ የጀመረው ከየካቲት 1998 የክልል ስብሰባ በኋላ ነው።

አቶ ወጋየሁ ደጋግመው ለአካባቢው ሹሞች አቤት ቢሉም ባመቱ መጨረሻ ምንም የተወሰደ እርምጃ የለም። " የወጋየሁ አቤቱታ ታይቶ በሕዝብ ተመራጩ ላይ የሚደረገው ወከባ እንዲቆም እርምጃው መቼ ይወሰዳል?

በሀምሌ 1998 በአንድ የኦሮሞ ንቅናቄ አባልና የአካባቢው የምክር ቤት ተመራጭና በሌሎች አምስት የኦሮሞ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት ፍርድ ቤት ውለው ሲመለሱ በፀጥታ ኀይሎች ተደብድበዋል። በተፈጠረው ክስተት ላይ ምንም ክትትል ሲደረግ አልታየም" በነዚህ በአካባቢው የምክር ቤት አባላት የደረሰውን የድብደባ ወንጀል አስመልክቶ የተደረገው ምርመራ ምን ላይ ደረሰ?

በኦርሚያ ክልል የሴራሮ አውራጃ የኦርሞ ብሔራዊ ጉባኤ (የተባበሩት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አባል) የነበረው አቶ አብደታ ዲታ አንቴሌ በ1997 ከደረሰበት ድብደባ በኋላ ሕይወቱን የአጠፋበት ጉዳይ ላይ ምንም እንቅስቃሴ አይታይም። በአብደታ ዲታ ኢንቴሌን የተፈፀመው የድብደባ ወንጀልና ብሎም የእራስን ማጥፋት ምርመራ ምን ደረሰ?

አዲሱ ምእተ አመት ከመግባቱ ቀደም ብሎ የፀጥታ ኃይሎች ያለምንም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከኦሮሚያ ክልል በርካታ ኦሮሞዎችን አስረዋል።

ከኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ጋር ግንኙነት አላችሁ፤ የሽብር እንቅስቃሴ ለመጀመርም እቅድ ሳይኖራችሁ አይቀርም በሚል ግምት 450 ሰዎች ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጉዳዩ የታሰሩ አንዳሉ አዲስ አበባ ላለው የተቃዎሚዎች ቢሮ ሪፓርት ተደርጓል። ከነዚህ ሶስቱ የነቀምቴ የኢትዮጵያ የሰው ልጆች መብት ኮሚሽን የስራ አስፈፃሚ አባላት ናቸው። የተያዙት በሙሉ ለፍርድ አልቀረቡም ወይንም ወንጀላቸው ይህ ነው ተብሎ አልተነገራቸውም። እስከ አመቱ መጨረሻ 148ቱ በእስር ላይ ናቸው። በኦሮሚያ ክልል 450 ሰዎች ለማሰር ምን መረጃ ተይዞ ነው? እስረኞቹ ለምን አልተለቀቁም ወይም በህጉ መሰረት ለምን ለፍርድ አልቀረቡም?

በ1998 በኦሮሞ ክልል በናዝሬት ከተማ በመደብር ባለቤቶችና በፓሊስ መካከል በተፈጠረ ግጭት የፀጥታ ኀይሎች 180 ሰዎችን አስረዋል። እስረኞቹ በመጀመሪያ የተከሰሱበት ወንጀል አመፅን ማነሳሳትና

ንብረትን ማውደም ሲሆን አብዛኛው ክሳቸው ፤በ1997 መጨረሻ ውድቅ ሆኖ ተለቀዋል። ሆኖም ግን ያልተለቀቁትን አስመልክቶ ምንም ወሬ የለም "ከ180ቹ ስንቱ እስር ላይ ናቸው? ግለሰቦቹ ለምን እስከአሁን በእስር ላይ ቆዩ? ሕግና ደንቡ በሚያዘው መሰረት ጉዳያቸው ለምን ወዲያውኑ አልታየም?

ከጀመረ አመት ያስቆጠረው በመንግስት ኀይሎችና "በኡጋዴን ነፃ አውጪ (በሱማሌ ክልል ዘርን መሰረት ያደረገ የአማፂያን ድርጅት) መካከል የሚካሄደው ጦርነት ሰፊ የሰው ልጅ መብት ረገጣን አስከትሏል። ግድያን፤ ግርፋትን፤ አስገድዶ መድፈርን እንዲሁም አፍኖ መውሰድን፤ ከሕግ ውጪ ማሰርን፤ መንደሮችን በማቃጠል ብዙዎች ከቀያቸው እንዲሰደዱና የምግብና የመዳህኒት ስርጭትም ለህዝቡ እንዳይደርስ አግዷል። "በሶማሌ ክልል ውስጥ የተፈፀመውን የግድያ፤ የድብደባ፤ የአስገድዶ መድፈር፤ የአፈና እና ከሕግ ውጪ ማሰርን፤ መንደሮችን ማቃጠልንና በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎችን የማፈናቀልን ወንጀል አስመልክቶ የተደረገ ምረመራ አለ ወይ? በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተከሶ ለፍርድ የቀረበ ሰው አለ?

"በምስራቅ  ወለጋ ዞን በጉዱሩ አውራጃ በ1998 ዓ.ም በፌዴራል ፓሊስ የተገደሉትን 15 የሰላማዊ ሰልፍ ተሳታፊዎችን አስመልክቶ ምንም የተደረገ ምርመራ የለም!  የአስራ አምስቱ ሰዎች በፌዴራል ፓሊስ መገደል ምርመራ ተደርጎበት ገዳዮች ለምን ለፍርድ አልቀረቡም? "ሕገ መንግስቱ እስረኞችን መደብደብና ማሰቃየት ቢከለክልም የፀጥታ ኃይሎች እስረኞችን እንደሚያሰቃዩ በርካታ ታማኝ ዘገባዎች አሉ። በአዲስ አበባው የማእከላዊ እስር ቤት የሚሰሩ መርማሪዎች እስረኞችን ለማሳመን ሕጋዊ ያልሆኑ የምርመራ ዘዴዎችን መጠቀም የተለመደ ተግባራቸው ነው። " በማእከላዊ እስር ቤት የሚካሄደው እስረኞችን የመደብደብና የማስቃየት ተግባር አብቅቶ አሰቃዮቹ ለፍርድ የሚቀርቡት መቼ ነው?

"ባለስልጣኖች በየጊዜው ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰዎችን በማሰር እስረኞቹ ከጠበቃና ከቤተሰብ እንዳይገናኙ ይከለክላሉ። በተለይም በገጠሩ አካባቢ ፓሊስ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የግል መኖሪያ ቤት ውስጥ ገብቶ ግለሰቦችን ማስሩን ቀጥሎበታል። በሚያዚያ 16 ቀን የዳሞት ወይዴ አወራጃ የፓሊስ አዛዥ መረዶ ሜጋ እና አልካል ዳብሶ ዲንጎ የተባሉትን ግለሰቦች ተኩሶ ገድሏል። ወንጀሉ የተፈፀመባቸው ግለሰቦች አውራጃቸው ከሌላ አውራጃ ጋር ይደባለቅ የሚለውን ውሳኔ በመቃወም በተደረገ

የተቃውሞ ሰልፍ ተከፋይ ነበሩ። እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ ግድያውን አስመልክቶ የተደረገ ምርመራ የለም። የሟች ቤተሰቦችም ተደጋጋሚ ዛቻና ማስፈራሪያ ከፓሊስ አዛዥ እየደረሰባቸው ነው። የመረዶ ሜጋ ገዳይ  የፓሊስ ሀላፊው ለፍርድ ይቀርባልን? በመረዶ ቤተሰቦች ላይ የሚደርሰው ወከባስ ያቆማልን?

''ሕጉ እንደሚያዘው ተከሳሾች ሳይዘገዩና ከአድልወ ነፃ በሆነ አሰራር በፍርድ ቤት የመዳኘት መብት አላቸው፤እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብትና ለመረጡት የሕግ አማካሪ ውክልናን የመስጠት መብት እንዲሁም ይግባኝ የማለት መብት አላቸው። እነዚህ ሁሉ የመብት ማስከበሪያዎች ተጥሰው ጉዳዮች በዝግ ችሎት ይካሄዳሉ። ባለስልጣናት ተከሳሾች ከጠበቃቸው እንዲገኛናኙ ብዙም አይፈቅዱላቸውም እንዲሁም ጨርሶም የማይፈቅዱበት ጊዜ አለ።  የዳኞች የብቃት ማነስ፤ ለረጅም ጊዜ የቀጠሮዎች መጓተት፤ ለቀልጣፋ አሰራር እገዛ የሚያደርግና በብቃት የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለመኖር  የፍርድ ቤት አሰራሩን እያጓተተው ነው።  ''ብዙውን ጊዜ እስረኞች ጥፋተኝነታቸው ሳይረጋገጥ ጥፋተኛ እንደሆኑ ተደረጎ ይወሰዳል።  በወንጀለኝነት የተከሰሰ ሰው ቀጠሮ ሳይንዛዛ ፍትህ ለምን አያገኝም? ለምንስ ሕጉ የሚፈቅድለት የተከሳሽ መብቶች ይነፈጉታል። ከከተማ ወጣ ባሉ አካባቢዎች ግለሰቦችን ከሕግ ውጪ ማሰር፤ ወንጀል ያልሰሩ ዜጎችን እስር ቤት ማጎርና ከቤተሰብና ከሕግ አማካሪ እንዳይገናኙ ማገድ የሚቀረው መቼ ነው?

<u>ክቡር አምባሳደር ሁላችንም ጆሮዎች ነን "በተዘረዘሩት ላይ አወያየን"</u>